# ልጇን “በእድሉ” ብላ ስም አወጣችለት”



የወለድነው ልጅ ሲታመም የምንይዘው፣ የምንጨብጠው እንደምናጣ እሙን ነው፡፡ በተለይ አንድ ፍሬ ልጅ ሲሆን ግራ ይገባል፡፡ ምክንያት እዚህ ጋር ነው የሚያመኝ ማለት አይችልም፡፡ እንግዲህ በዚህ ሁኔታ ያለ ልጅ እናት ታቅፋው ሀኪም ቤት ደርሳ እየተመለሰች ነው፡፡ ቶሎ ይሻለው ይሆን እያለች ሀሳብ ገብቷታል፡፡ ከጀርባ የታዘለው ልጅ ህመሙ አድክሞት እንቅልፉን እየለጠጠ ነው፡፡

ወደ ቤት እየተጓዙ እያለ አንድ ልጅ እግር ቢጤ ሎተሪ ካልገዛሽኝ አላት፡፡ ከልጇ ህክምና የተረፉ የተወሰኑ ብሮች መካከል አስር ብር አውጥታ ትገዛለች፡፡ በእንቅርት ላይ እንዲሉ ደሞ ኑሮዋ ምሬቱን እያበዛ ነው፡፡ ከዚህ ኑሮ ወደ ውጪ ለመጥፋት ድረስ አስባለች፡፡

በሌላ ቀን ከመንገድ ስትመለስ ከዚህ በፊት የገዛቻውን ሎተሪ አውጥታ ለሎተሪ አዟሪው ታሳያለች፡፡ የ2002 ቶምቦላ ሎተሪ 10ኛ ዕጣ ዕድለኛ መሆኗን ትረዳለች፡፡ዕድለኛዋ ሶፍያ ቲቶ የ1050 ሲሲ የቤት አውቶሞቢል እና የ20,000 ብር ዕድለኛ ሆናለች ፡፡ነዋሪነቷ በዝዋይ ደጀገል በሚባል ቦታ ነው፡፡ የሚገርመው ዕድለኛዋ ከዛሬ 10 ዓመት በፊት 10,000 ብር ዕድለኛ ነበረች፡፡ ባገኘችውም ብር በገጠር ቤት እንደሰራችና ለችግሯ እንደደረሰላት ታስተውሳለች፡፡ ስለዕድሏም ስትገልጽ ከጨለማ ወደ ብርሃን እንደ መወጣት ነው ብለላች፡፡ ሎተሪው ከመውጣቱ ከሁለት ወር በፊት የተወለደው ልጅ ስሙ ብሮምሳ የነበረ ሲሆን አሁን በዕድሉ ብለዋለች፡፡